


# የቩዚ እህት እንደተናገረችው


- Nina Orange
- Wiehan de Jager
- Dawit Girma
- amharisk
- nivå 4



አንድ ቀን ጠዋት ቡዚን አያቱ ጠሩትና፣ ‹‹ቡዚ፣ እንካ ይህንን እንቁላል ለወላጆችህ ውሰድላቸው። ለእህትህ ሰርግ ትልቅ ኬክ መስራት ይፈልጋሉና›› አሉት።



ወደ ወላጆቹ ዘንድ እየሄደ እያለ ቩዚ ሁለት ልጆች ፍራፍሬ ሲለቅሙ አገኘ። አንደኛው ልጅ የቩዚን እንቁላል ወሰደና ወደዛፉ ወርውሮ አጋጨው። እንቁላሉም ተሰበረ።



‹‹ምንድነው ያደረከው?›› አለ ብዙዓየሁ እያለቀሰ። ‹‹እንቁላሉ እኮ ለኬክ መስሪያ ነበር። ኬኩ ደግሞ ለእህቴ ሰርግ ነበር። አሁን እህቴ የሰርግ ኬክ አለመኖሩን ስታውቅ ምን ትላለች?››



ልጆቹ ቩዚን በማናደዳቸው አዘኑ። ‹‹እንግዲህ ኬኩን በመስራት ማገዝ አንችልም፤ ቢሆንም ግን ለእህትህ የሚሆን ምርኩዝ ይሄው›› አለ አንደኛው። ቩዚ ጉዞውን ቀጠለ።



እየተጓዘ እያለም ሁለት ሰዎች ቤት ሲሰሩ አገኘ፡፡ ‹‹ይሄን ጠንካራ ምርኩዝ መጠቀም እንችላለን?›› ጠየቀ አንደኛው፡፡ ነገር ግን እንጨቱ ለግንባታ የሚሆን ጠንካራ ስላልነበር ተሰበረ፡፡



‹‹ምን ማድረጋችሁ ነው?›› ቩዚ አለቀሰ። ‹‹በትሩ እኮ ለእህቴ ስጦታ ነበር። ፍራፍሬ ለቃሚዎቹ የኬክ መስሪያውን እንቁላል ስለሰበሩብኝ በምትኩ የሰጡኝ ነበር። ኬኩም ለእህቴ ሰርግ ነበር። አሁን ግን ምንም እንቁላል፣ ኬክም ሆነ ስጦታ የለም። እህቴ ምን ትል ይሆን?››



አናጺዎቹም በትሩን ስለሰበሩበት አዘኑ። ‹‹እንግዲህ ኬክ በመስራት አላገዝናችሁም፤ ባይሆን ይህ የቤት ክዳን ለእህትህ ይሁን›› አለ አንደኛው። ኹዚም መንገዱን ቀጠለ።




በመንገዱም ላይ፣ ቩዚ አንድ ገበሬና ላም አገኘ። ‹‹እንዴት ጣፋጭ ቄጤማ ነው፣ እንደው ጥቂት መብላት እችል ይሆን?›› ላሟ ጠየቀች። ቄጤማውም ጣፋጭ ስለነበረ ላሟ ሁሉንም በላችው።



‹‹ምን ማድረግሽ ነው?›› ቡዚ አለቀሰ። ‹‹ቄጤማው እኮ ለእህቴ ስጦታ ነበር። አናጺዎቹ ምርኩዜን ስለሰበሩ በምትኩ የሰጡኝ ነበር እኮ። ምርኩዙንም ፍራፍሬ ለቃሚዎች እንቁላሌን በመስበራቸው ምክንያት በምትኩ የሰጡኝ ነበር። እንቁላሉም ለእህቴ ሰርግ ነበር። አሁን እንቁላል የለም፣ ኬክም የለም፣ ስጦታም የለም። እንግዲህ እህቴ ምን ትል ይሆን?››



ላሟም ተስገብግባ ስለበላችበት አዘነች። ገበሬውም ላሟ ለሹዚ እህት ሰርግ ስጦታ ሆና እንድትሄድ ተስማማ። ስለሆነም ሹዚ ተሸከማት።



ነገር ግን ላሟ ወደገበሬው ዘንድ ተመልሳ እየሮጠች ሄደች። ቩዚም ባዶውን ቀረ። ከእህቱም ሰርግ በጣም ዘግይቶ ደረሰ። እንግዶቹም መመገብ ጀምረው ነበር።



‹‹ምን ይሻለኛል?›› አለ ሹዚ እያለቀሰ። ‹‹ሮጣ የሄደችው ላም ስጦታ ነበረች፣ አናጺዎቹ በሰጡኝ ቄጤማ ፋንታ። አናጺዎቹም ቄጤማውን የሰጡኝ ፍራፍሬ ለቃሚዎቹ የሰጡኝን በትር ስለሰበሩብኝ ለዛ ማካካሻ ነበር። ፍራፍሬ ለቃሚዎቹ በበኩላቸው ያንን በትር የሰጡኝ ለሰበሩብኝ የኬክ ማዘጋጃ እንቁላል ምትክ ነበር። ኬኩ ደግሞ ለሰርጉ ነበር። አሁን እንቁላል የለም፣ ኬክም የለም፣ ስጦታም የለም።››



የቩዚ እህትም ትንሽ አሰብ አደረገችና እንዲህ አለች፦ ‹‹ወንድሜ ቩዚ፣ ስለስጦታ ምንም ግድ የለኝ። ስለኬክም ቢሆን እንዲሁ! ሁላችንም እዚህ በአንድ ላይ አለን። በዚህም ደስተኛ ነኝ። አሁን የክት ልብስህን ልበስ እና ይህን ቀን እናክብር!›› እናም ቩዚ ያደረገው ይህን ነበር።

# Barnebøker for Norge

barneboker.no

## የሹዚ እህት እንደተናገረችው

Skrevet av: Nina Orange
Illustret av: Wiehan de Jager
Oversatt av: Dawit Girma

Denne fortellingen kommer fra African Storybook (africanstorybook.org) og er videreformidlet av Barnebøker for Norge (barneboker.no), som tilbyr barnebøker på mange språk som snakkes i Norge.

Dette verket er lisensiert under en Creative Commons
Navngivelse 3.0 Internasjonal Lisens.